በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ጥቅምት ፳፱ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

መግቢያ

- አሕዛብ በዓመፀኝነታቸው የሠሩት ኃጢአትና የአምላካችንም ማዳኑ እንዳስፈለጋቸው በሮሜ ምዕራፍ 1 ተጽፎልናል፡፡ በምዕራፍ 2 ደግሞ አይሁድ የሠሩት ኃጢአትና ሕጉን በመንፈስቅዱስ ረዳትነት ካልሆነ ሊፈጽሙት የማይችሉት መሆኑ እንዲሁም ለእነርሱም ማዳኑ እንዴት እንዳስፈለጋቸው ተጽፎልናል፡፡
- አይሁድ እግዚአብሔርን ስለሚያውቁ፣ ሕግና ቤተመቅደስ ስለነበራቸው በአሕዛብ ይፈርዱ ነበር፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስም አንተ በሌላው የምትፈርድ የምታመካኘው የለህም በማለት መልዕክቱን ጀመረ፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ይልቁኑ በተመሳሳይ ኃጢአት የምንገኝ ሆነን በሌላው ስንፈርድ አድልዎ በሌለበት በእግዚአብሔር ፍርድ ሥር እንደምንወድቅ ፍርዱም በሥራችን የሚፈረድ ፍርድ እንደሆነ ጻፈ፡፡
- አሕዛብም በተፈጥሮ ወይም በሕገ ልቦና ተመርተው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ባለማድረጋቸው እንደሚፈረድባቸው፣ አይሁድም ነቢያትና ሕጉ ቢኖራቸውም ለስሙ ሳይገዙ እግዚአብሔርን ሳያከብሩ ፈራጅና ትምክህተኛ ሆነው በሌላው በሚፈርዱት ፍርድ እንደሚፈረድባቸው ገለጠ፡፡
- አይሁድም ሥጋ የለበሰውን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን ካላመኑ ከፍርድ እንደማያመልጡ ጻፈላቸው፡፡
- ምዕራፉም ሲተቃለል እውነተኛ ክርስቲያን አይሁዳዊ ልቦናው የተገረዘ እንጂ በሥጋ የተገረዘ ብቻ አለመሆኑ ተጠቅሷል፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

**ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 2**

- 2፡1 አይሁድ ቤተ መቅደሱ፣ የኪዳኑ ታቦት፣ ቃል ኪዳኑ፣ … ስለነበራቸው ራሳቸውን ከሌላው የተሻለ አድርገው ያስቡ ስለነበር ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ባለው ነገር እየተመኩ በሌላው የሚፈርዱ ከእግዚአብሔር ፍርድ እንደማያመልጡ ጻፈ፡፡
- ብዙ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ያልጸና ፍድር የሚፈርዱ ሰዎች በሌላው የሚፈርዱት ራሳቸው ኃጢአቱን እየሠሩት ስለሆነ የሚሠሩት ሥራና የሚፈርዱት ፍርድ ይለያያል፡፡ እነዚህም በተመሳሳይነት በሠሩት ሥራ በራሳቸው ስለማይፈርዱ (Inconsistency) በእግዚአብሔር ይፈረድባቸዋል፡፡
- 1፡2 በውጪ ለሚመለከት ሰው ራስን የሕጉ ፈጻሚ አስመስሎ ማቅረብ እግዚአብሔርን ማታለል የሚያስችል ስልት አለመሆኑን እግዚአብሔርም የተሰወረውን ገልጦ የሚፈርደብን እንደሆነና ተደብቆም የሚቀር ነገር እንደሌለ ጻፈ፡፡
- አስመሳዮች በራሳቸው የሚፈርዱ ሲሆኑ ኃጢአተኛው ሁሉ በእውነት በእግዚአብሔር የሚፈረድበት መሆኑ ተገልጧል፡፡
- 1፡3 ከኃጢአታችን ነጻ የምንወጣበትን ይቅርታን የምናገኝበትን ሌላ ምክንያት ሲገልጽልንም አንዳንዶች ተራ ምክንያቶች ያላቸው ተራ ፈራጆች መሆናቸውንና ይህን ኃጢአት የሚሠሩትን ብቃወም ብፈርድባቸውም እጸድቃለሁ ብለው ማሰባቸውንም ተናገረ፡፡ ያንኑ ተመሳሳይ ነገር ብናደርግም በመቃወማችንና በመፍረዳችን እግዚአብሔር እውነትንና ሐሰትን ለይተው ያውቃሉ ብሎ ሳይፈርድብን እናመልጣለን ይላሉ፡፡ ይህም ሞኝነት ነው፡፡ በሌላው ስለፈረድን ከፍርድ የምናመልጥ ይመስለናል?

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

**ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 2**

- 2፡4 አንዳንዶች እግዚአብሔር እንደ ሐናንያና ሰጲራ *የሐዋ 5፡1-11፡፡* እግዚአብሔር ስህተቴን ተቀብሎታል ብለው ያስባሉ፡፡ አይፈርድብኝም በሚልም አስተሳሰብ ተመሳሳይ ኃጢአቶችን በመፈጸም ይቀጥላሉ፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ግን እግዚአብሔርን ሳይፈርድብን መታገሱ፣ ዕድሜ ሰጥቶ መጠበቁ ለንስሐ የተሰጠን ዕድል መሆኑን መረዳት እንጂ ቸል ማለት እንደማይገባ ካልሆነ ግን እግዚአብሔርን እንደመናቅ እንደሚቆጠርብንና አላዋቂነታችንንም እንደሚገልጥብን ጻፈ፡፡
- 2፡5 በሥርዓተ አልበኝነት የተነሳ የተሰጠንን ዕድል ካልተጠቀምንበት የእግዚአብሔር ቁጣው በእኛ ላይ እንደሚሆን ያልረጋ ሰው በራሱ የሚፈርድ መሆኑን፣ አስመሳይ ሰው በእውነት የሚፈረድበት መሆኑን፣ ሞኝ ሰውም ሥራው ተገልጦ እንደሚፈረድበትና፣ ሥርዓተ አልበኛ - ሕግን የሚተላለፍ ግን የእግዚአብሔርን ቁጣ በራሱ ላይ እንደሚያነሳሳነ የሚያስረዱ ነጥቦችን በማስቀመጥ ይቅርታን እንደማናገኝ ጻፈልን፡፡
- ንስሐ ሳይገባ የሚኖር ሰው የእግዚአብሔርን ቸርነቱን የናቀና ልቦናው የደነደነ መሆኑን ሲጽፍልን ያስታወሰን ፈርዖንን ነው፡፡ እግዚአብሔር ዐሥር ዕድሎችን በመስጠት ፈርዖንን ታግሶታል፡፡ እርሱ ግን ልቦናው ኃጢአትን የሚወድ ሆኖ ደነደነ፡፡
- እንዲህ ያለ ሰው የፍርድ ቀንን የእግዚአብሔር ቁጣ በራሱ ላይ ያነሳሳል፤ እግዚአብሔርን ራርቶ እንዳይፈርድለት ሳይሆን ጨክኖ እንዲፈርድበት ያደርጋል አለን፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

## ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 2

- የእግዚአብሔር ፍርድ መታወቂያ ምልክቶች አሉት፡፡ እነርሱም፡-
    1. ፍርዱ እውነተኛ መሆኑ፡፡ ‹‹የወደድከውን እመን በመጨረሻም እንደእምነትህ ይፈረድልሃል›› የሚሉ አሉ፡፡ እኛ ግን ማመን ያለብን ፍጹምና ብቸኛ የሆነውን አንድ እውነት እንጂ የፈለግነውን አይደለም፡፡ እውነትም እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ *ዮሐ 1፡፡*
    2. በታጋሽነቱ የንስሐ ዕድል ከተሰጠን በኋላ የሚፈጸም ነው፡፡፡
    3. አድልዎ የሌለበት ቅንና የጽድቅ ፍርድ ነው፡፡ በዚህ ዓለም ብዙ ጊዜ ፍትሐዊነት የለም፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ፍርድ ግን ቅንና ፍትሐዊ ነው በማለት ያስታወሰው አብርሃምን ነው፡፡ አብርሃም በሰዶምና ገሞራ ሃምሳ ሰው ቢጠፉ ነውን የምታጠፋት ብሎ ቢጠይቅ … አብርሃም ሆይ ሃምሳ ሰው ካገኘህ ሄደህ ቁጠር ካገኘህም እምራለሁ… በማለት ቢፈቅድለትም አሥር ሰዎችም ማግኘት እንዳልተቻለ ሎጥና ሁለቱ ልጆች ብቻ እንደተረፉ በማሳየት ፍርዱ ቅንና ፍትሐዊ እንደሆነ አስረድቷል፡፡ *ዘፍጥ 18፡17-ፍጻሜ፡፡*
    4. እንደ ሥራችን የሚፈርድ መሆኑ፡፡ እግዚአብሔር የሥራን አስፈላጊነት ነገረን እንጂ እመንና የምትፈልገው ሥራ ወይም እመን እንጂ ሥራ አያስፈልግም እንደሚሉ ፕሮቴስታንቶች አላለንም፡፡ እግዚአብሔር ጥሩም ሆነ መጥፎ እንደሥራችን ይፈርዳል፡፡
    5. ያለ አድልዎ ይፈርዳል፡፡ እንደ ሥራ ይፈርዳል እንጂ በዘር፣ በጾታ፣ በዕድሜ አድልዎ አያደርግም፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 2

- የእግዚአብሔር ፍርድ መታወቂያ ምልክቶች አሉት፡፡ እነርሱም፡-
  6. በሰጠን ሕግ ይፈርዳል፡፡ እግዚአብሔር ሕገ ልቦና፣ ሕገ ኦሪትንና ሕገ ወንጌልን ለሰው የሰጠ እንደመሆኑ እንደ ሕጋቸው ይፈርዳል፡፡ በሕገ ወንጌል ከሆነው የመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት በቀር ሕግን ሊፈጽም የሚቻለው የለም፡፡
     - የመዳን ወይም የወንጌል ሕግ ሰውን ፍጹም ነጻ የሚያደርገው ነው፡፡ ለምሳሌ በሙሴ ሕግ ባልንጀራህን ውደድ ይቅርም በለው ጠላትህን ግን ጥላ ተብሎ የተጻፈ ሲሆን በወንጌል ግን ደረጃው ከፍ ብሎ ‹‹ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና፡፡ …›› ***<u>ማቴ 5፡44-45</u>*** ተሰጠን፡፡
     - የሕጉ መርሕ ተመሳሳይ ቢሆንም አተገባበሩ ግን ይለያል፡፡ አይሁድ የቀለለውንም መፈጸም አልቻሉም፡፡ ታዲያ በመንፈስቅዱስ ረዳትነት ካልሆነ ወዳጃቸውን ይቅር ማለት የተሳናቸው አይሁድ ጠላቶቻቸውን ይቅር ይሉ ዘንድ እንዴት ይችላሉ?
  7. በውጪ በማሳመሰል በያዝነው ሕይወት ሳይሆን የተሰወረውን ገልጦ ይፈረዳል፡፡
- በአጠቃላይ ሰባቱ የፍርዱ መታወቂያዎች እውነት ሮሜ 2፡2፣ ትዕግሥት ሮሜ 2፡4፣ ቅን ሮሜ 2፡5፣ ሥራችን ሮሜ 2፡6፣ ያለ አድልዎ ሮሜ 2፡11፣ እንደ ሕጋችን ገልጦ ሮሜ 2፡12 ናቸው፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

**ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 2**

- 2፡6-7 እንደ ሥራችን ይፈርዳል፡፡ መልካሙን ነገር ለጽድቅ የሆነውንም ሥራ ማድረግ ከወደድን መታገስ እንደሚገባንና የጀመርነውንም መቀጠል እንደሚገባ ጻፈልን፡፡ መልካም ሥራን የምንሠራው ሌሎችን ለመማረክ ወይም ለታይታ ሳይሆን ከአምላካችን ከእግዚአብሔር የሚደረግልንን ምስጋናና ክብር ፈልገን ነውና ታገሡ አለን፡፡
- የመልካም ሥራ ሽልማትም ዘላለማዊ ሕይወት መንግሥተ ሰማያት ናት፡፡
- ለሁሉም ምርጫው የራሳችን ከመሆኑ ጋር መልካም ሥራ ትዕግሥትንና የጀመሩትን መቀጠል እንደሚፈልግ ነገረን፡፡
- 2፡8 ከታይታም ጋር ራሳቸውን ብቻ የሚወዱ እውነትን መቀበል እንደሚከብዳቸውና መጨረሻቸውም የእግዚአብሔር ቁጣና መቅሰፍት እንደሆነ ተገለጸልን፡፡
- 2፡9 ክፉን የሚያደርጉ መከራና ጭንቀት እንደሚሆንባቸውና አይሁድ አስቀድመው የተከተሉ እንደመሆናቸው በቅድሚያ እንደሚፈረድባቸው ነገረን፡፡
- 2፡10 መልካምን ለሚያደርጉ አይሁድም ሆነ አሕዛብ ምስጋና፣ ክብርና ሰላምታ ይገባቸዋል አለን፡፡
- 2፡11 እግዚአብሔር አድልዎ የሌለበት አምላክ እንደሆነ ተነገረን፡፡
- 2፡12 አሕዛብ በሕገ ልቦና የተሰጣቸውን አልጠበቁም እግዚአብሔርንም አላወቁትምና ያለ ሕግ ይቀጣሉ፡፡ ዮሴፍ ኃጢአትን ከመሥራት የራቀው በሕገ ልቦና ነው፡፡ በሕግ የሚኖሩም አይሁድ በሕግ ይቀጣሉ፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

## ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 2

- አሕዛብ ያለሕግ ይጠፋሉ፤ አይሁድም በሕግ ይፈረድባቸዋል፡፡ መርዝ እንዳለበት የተነገረንን ምግብ መብላት መግደሉ አይቀርም መበላት እንደሌለበትም እየተነገረ መብላትን መቀጠል የበለጠ ያስቀጣል፡፡ ‹‹እውነት እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶምና ለገሞራ አገር ይቀልላቸዋል፡፡›› *ማቴ 10፡15፡፡* የተባለበት ምክንያት ጌታችን በቅፍርናሆም አስተምሮ አናምንም ብለዋል ሰዶምና ገሞራ ግን በሕገ ልቦና ጊዜ ጠፍተዋልና እንደተሰጠ ዕድል መሠረት ይቀጣሉ አለን፡፡
- 2፡13 አይሁድ ሕግ ያላቸው መሆኑን በማስታወስ ብቻ ይመኩ ነበር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም የሚያጸድቀው ሕግን ማወቅ ወይም መስማት ሳይሆን መፈጸም ነውና ካልፈጸማችሁ አትጸድቁም አለ፡፡
- 2፡14 ሕግ ለሌላቸው በልቦናቸው የተጻፈ ሕግ በልምምድ እንደሚያድግ
- 2፡15 በልቦና የተጻፈውም ሕግ በተፈጥሮ እየመራን ሊያካስሰን ወይም ሊያመካኝ ይችላል፡፡
- 2፡16 እግዚአብሔርም በአይሁድም ሆነ በአሕዛብ በሁሉም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ይፈርዳል፡፡ ይህም የመለኮታዊ አምላክነቱ ምስክርነት ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስም ሲፈርድ የተሰወረውን ገልጦ ነው፡፡
- 2፡17-20 የአይሁድ በደላቸውንና ማዳኑም የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በዝርዝር ተጽፎአል፡፡
- አይሁዳዊ አድርገህ ስለፈጠርከን እናመሰግንሃለን ብለው በዘራቸው፣ በሕጋቸው… እውነተኛውን አምላክ የምናመልክ ነን ብለው ተመኩ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ማወቅና መመካት ባወቁት እውነት ካልኖሩበት የእግዚአብሐየርን ፈቃድ ካላደረጉበት ምን ይጠቅማል? አለ፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

**ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 2**

- በሕግም የእውቀትና የእውነት መልክ ስላለህ፥ የዕውሮች መሪ፥ በጨለማም ላሉ ብርሃን፥ የሰነፎችም አስተማሪ፥ የሕፃናትም መምህር እንደ ሆንህ በራስህ ብትታመን በቃሉ ሕይወትነት መመራት ችግርህ ነውና ምን ይረባሃል?
- 2፡21-22 አትስረቅ፣ አትዋሹ፣ አታመንዝሩ፣ … የምትልና የምትሰብክ ትሰርቃለህ፣ ትዋሻለህ፣ ታመነዝራለህን፡ ጣዖታትን የምትጸየፍ ቤተ ጣዖትን መሥራት ግን ችግር የለውም ትላለህን?
- 2፡23-24 ሕጉን ስናፈርስ እግዚአብሔርን እናሳፍረዋለን… በኢሳ 52፡5 እና ሕዝ 36፡22 እንደተጻፈው ስሙ በአሕዛብ መካከል ይሰደባል፡፡ ‹‹ወገኔ በከንቱ ተወስዶአልና አሁን ከዚህ ምን አለኝ? ይላል እግዚአብሔር የሚገዙአቸው ይጮኻሉ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ ስሜም ሁልጊዜ ቀኑን ሁሉ ይሰደባል፡፡››፣ ‹‹ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የእስራኤል ቤት ሆይ፥ በመጣችሁባቸው በአሕዛብ መካከል ስላረከሳችሁት ስለ ቅዱስ ስሜ ነው እንጂ ስለ እናንተ የምሠራ አይደለሁም፡፡››
- 2፡25 አንዱን ሕግ ጠብቆ ሌላውን ማፍረስ አልተፈቀደም፡፡ መገረዝን መጠበቅ የሚያጸድቀው ሌሎቹን ሕጎች ሁሉም በመጠበቅ ነው፡፡ ሌሎችን ሕጎች እየጣሱ መገረዝን ብቻ መጠበቅ አሕዛብን መምሰል ነው - ጥምቀት የሆነው ግዝረት የሚጠቅመን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስንፈጽምና እንደ ፈቃዱ ስንኖር ነው፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

**ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 2**

- 2፡26 ሕግን አለመጠበቅ እንደ አሕዛብ መሆን ነው፡፡
- 2፡27 በፍርድ ቀን ሕግ ያላቸው ሕግ የሌላቸው ሆነው በሕገ ልቦና የተመሩት በፈጸሙት በጎነት አንጻር ይፈረድባቸዋል፡፡
- 2፡28 ጽድቅ ከአይሁድ ወይም ከክርስቲያን ወገን በመወለድ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ ሕጉንም በመፈጸም በክርስትናው ትምህርት እየተመሩ በመኖር ነው፡፡
- 2፡29 ውጪያችሁን ሳይሆን ውስጣችሁን አሳምሩት፡፡ በውጪ እየወደድን በውስጥ የምንጠላ ከሆንን እግዚአብሔር የውስጡን እግዚአብሔር ገልጦ አውቆ ይፈርድብናልና የልቦናችንን ነውር ሁሉ ቆርጠን እንድንጥል ልቦናችንን እንድንገርዝ መገረዙም በመንፈስ ቅዱስ የሆነ እንደሆነ ተነገረን፡፡
- በውስጥ ያለውን ነውር ሁሉ ቆርጦ በመጣል ሊለውጠን የሚችለው መንፈስቅዱስ እንደሆነና ትኩረታችንንም ውጪን ወደ ሚመለከተው ሰው ሳይሆን የውስጡን መርምሮ ወደሚፈርድ እግዚአብሔር እንድናደርግ አለን፡፡
- በርካታ ሰዎች በሰው ፊት በ‹‹መልካምነት›› ተፈርዶላቸው በእግዚአብሔር ፊት ግን በበደላቸው ተከሰው ተፈርዶባቸዋል፡፡ ስለዚህ በማን ፊት እንዲፈረድልን እንወዳለን? ምስጋና ሁሉ ከእግዚአብሔር እንዲሆንልን እንትጋ በማለት ሐዋርያው ጻፈልን፡፡

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org